# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ገቢ የሚሰበስቡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ አያያዝና ትልልፍ መመሪያ ቁጥር 128/2013

የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን በማጠናከር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ እና ለተገልጋዩ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና በአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ባለሥልጣን በተናጠል ሲከናወን የነበረው የግብር /ታክስ/ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት ገቢዎች አሰባሰብ በአንድ ተቋም እንዲከናወን ተወስኗል፡፡

በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረጉት የሁለትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት መሰረት በአዲስ መልክ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከግብር ከፋዮች ግብር/ታክስ እና የማዘጋጃ ቤት ገቢዎች ሲሰበስቡ እንዲሁም የተሰበሰውን ገቢ ለገቢው ባለድርሻ ሲያስተላልፉ የሂሳብ አመዘጋገቡ የሚመራበትን ስርዓት ለመወሰን የአዲስ አበባ አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረጉት የሁለትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት አንቀጽ 4/2 ፊደል ተራ (ሠ) እና (ሰ) መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢን የሚሰበስቡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የገቢ ሒሳብ አያያዝ እና ትልልፍ" መመሪያ ቁጥር128/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

### 2. ትርጓሜ

1) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
2) "ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየክፍለ ከተሞች የተቋቋሙ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡
3) "ሴክተር መ/ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጀት የሚተዳደሩ የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶች ናቸው፡፡
4) "ሦስተኛ ወገኖች" ማለት ቀደም ሲል ከከተማ አስተዳደሩ ጋር ውል ገብተው የከተማ አስተዳድሩን ግብር፣ ታክስና ሌሎች ገቢዎች በውክልና የሚሰበስቡ ባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፡፡
5) "የገቢ ሒሳብ አያያዝ እና ትልልፍ" ማለት ገቢ ተሰብስቦና ተይዞ ለባለድርሻዎች የሚተላለፍበትና የሚመዘገብበት ሂደት ነው፡፡

### 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ግብር ከፋዮችን በሚያስተናግዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወረዳዎች እና ክፍለ ከተማዎች በተቋቋሙ የባለሥልጣኑ የማይክሮ፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የፌዴራል ግብር

ከፋዮች በሚስተናገዱባቸው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የባለሥልጣኑ የአገር ውስጥ ታክስ ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለባንክ ሒሳብ፣ ደረሰኝ እና ቅድመ ታክስ ክፍያ

### 4. የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት

1) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወረዳዎች የተቋቋሙ የማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በየዕለቱ የሰበሰቡትን ገቢ በቀጣዩ ቀን በቀጥታ ለየክፍለ ከተማው አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ ያደርጋሉ፡፡ ስለሆነም ለነዚህ ቅ/ጽ/ቤቶች የገቢ የባንክ አካውንት አይከፈትላቸውም፡፡

2) በየክፍለ ከተማው የሚደራጁትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው የአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በስማቸው የሚከተሉት የባንክ አካውንቶች ይከፈቱላቸዋል፡፡

   (ሀ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ገቢ የባንክ አካውንት (Depositary Account)

   (ለ) የአደራ የባንክ አካውንት (በአመቱ መጨረሻ የማይዘጋ)

3) ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች ገቢ የሚሰበስቡ የፌዴራል ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መካከለኛ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በስማቸው የሚከተሉት የገቢ የባንክ አካውንቶች ይከፈቱላቸዋል፡፡

   (ሀ) ለቼክ መመንዘሪያ የሚሆን የባንክ አካውንት፣

   (ለ) የአደራ የባንክ አካውንት /በዓመቱ መጨረሻ የማይዘጋ/፣

   (ሐ) የፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ አካውንት፣

   (መ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ አካውንት(Depositary Account)፣

(ሠ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ /Retention/ የሚቀመጥበት የባንክ አካውንት /በዓመቱ መጨረሻ የማይዘጋ/፣

## 5. የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ

1) የወረዳ ማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች፣ የክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች እስከ 2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለገቢ መሰብሰቢያነት የሚጠቀሙበትን ደረሰኝ (የማንዋልም ሆነ በኮምፒዩተር የሚታተም) ከየክፍለ ከተማው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በመረከብ ይጠቀማሉ፡፡ ከቀጣዩ በጀት ዓመት ጀምሮ ግን እነዚህ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚጠቀሙት ባለሥልጣኑ የሚያሳትመውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ይሆናል፡፡

2) ሦስተኛ ወገኖች እስከ 2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለገቢ መሰብሰቢያነት የሚጠቀሙበትን ደረሠኝ ከክፍለ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በመረከብ ይጠቀማሉ፡፡ ከቀጣይ በጀት አመት ጀምሮ ግን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሠኝ የሚረከቡት ከባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3) የወረዳ ማይክሮ እና የክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የሦስተኛ ወገኖች እስከ 2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ለገቢ መሰብሰቢያነት የተረከቡትን ደረሰኝ የተሰራበትንና ያልተሰራበትን በመለየት ለየክፍለ ከተማው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያስረክባሉ፡፡ ጽ/ቤቱም ቀደም ሲል የተሰበሰበው ግብር በትክክል ለቢሮው ገቢ ስለመደረጉ ኦዲት በማድረግ አረጋግጦ ደረሰኞቹን ይረከባል፡፡

## 6. የቅድመ ታክስ ክፍያ (Withholding Tax) አሰባሰብ

1) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወረዳና የክፍለ ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ያደረጉትን ግብር/ታክስ ለክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋሉ፡፡

2) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማዕከል ሴክተር መ/ቤቶች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ያደጉትን ግብር/ታክስ ለአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋሉ፡፡

3) ሴክተር መ/ቤቶች ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ያደረጉትን ግብር ገቢ ሲያደርጉ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች ተቀናሽ ያደረጉትን እና ከሌሎች ክልሎችና ከፌዴራል ግብር ከፋዮች ተቀናሽ ያደረጉትን ለብቻ ለይተው በሁለት ቼክ በማዘጋጀት ገቢ ያደርጋሉ፡፡

4) ቁራዎች ድርጅት ከግብር ከፋዮች ቀንሶ የሚያስቀረውን እና የሚሰበስበውን ግብር/ታክስ ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋል፡፡

5) የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁራዎች ድርጅት በኩል ተሰብስቦ ገቢ የተደረገለት ገቢ ከየግብር ከፋዮች የታክስ አካውንት እንዲቀናነስ መረጃውን ለሚመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያስተላልፋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የገቢ አሰባሰብ፣ ትልልፍ እና ሂሣብ አመዘጋገብ

### 7. በቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበ ገቢ ትልልፍ

1) በየወረዳው የተቋቋሙ የማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በየዕለቱ የሰበሰቡትን ገቢ /በጥሬ ገንዘብና በቼክ/ በማግስቱ ለክፍለ ከተማው አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ያስተላልፋሉ/ያስረክባሉ፡፡ ርክክቡ የሚፈጸመው የገቢው ሂሳብ ትክክለኛነት ተረጋግጦ ይሆናል፡፡ ለወረዳው ማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በቼክ የሚፈፀም ክፍያ ለክፍለ ከተማው አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት አካውንት ገቢ የሚደረግ ተብሎ መጻፍ አለበት

2) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮችን የሚያስተናግዱ በየክፍለ ከተማው የተቋቋሙ የአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች

(ሀ) የሰበሰቡትን ገቢ፣ ከየወረዳው ማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የተረከቡትን ጨምሮ በየዕለቱ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋሉ።

(ለ) ከላይ በተራ ፊደል "ሀ" በተገለፀው መሠረት ወደ ከተማ አስተዳደሩ ገቢ የባንክ ሂሣብ ገቢ የተደረገው ገንዘብ ወዲያውኑ ወደ ከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የባንክ ሂሣብ ይተላለፋል፡፡

(ሐ) ሰብስበው በአደራ የባንክ ሂሣብ ካስገቡት ገንዘብ ውስጥ ከክልል ግብር ከፋዮች ተቀናሽ የተደረገውን ባለድርሻውን በዝርዝር በመለየት ለገቢ ሂሣቦች ዳይሬክቶሬት፣ ከፌዴራል ግብር ከፋዮች የተቀነሰውን ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢው ከተሰበሰበበት ወር መጨረሻ ጀምሮ በ10 ቀን ጊዜ ውስጥ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

3) ከአዲስ አበባ ግብር ከፋዮች ገቢ የሚሰበስቡ የፌዴራል መንግስት ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መካከለኛ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ገቢ በሚከተለው አኳኋን ያስተላልፋሉ፣

(ሀ) የሚሰበሰበው ገቢ የፌዴራል ብቻ ተለይቶ በአንድ ቼክ ክፍያ ሲቀርብ ገቢው ቀጥታ ለፌዴራል መንግስት ተብሎ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡

(ለ) የሚሰበሰበው ገቢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ ተለይቶ በአንድ ቼክ ክፍያ ሲቀርብ ገቢው ቀጥታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተብሎ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡

(ሐ) የፌዴራል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የክልሎች ገቢ በአንድ ላይ በአንድ ቼክ ግብር ከፋዩ ካቀረበ እንዲሁም የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ በቅ/ጽ/ቤቱ ወደተከፈተው የቼክ መመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ ገቢ ከሆነ በኋላ ወዲያው ቼኩ ተመንዝሮ የክልሎችን ድርሻ ወደ አደራ የባንክ ሂሳብ፣የፌዴራልን ወደ ፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሳብ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ገቢ ለከተማ አስተዳደሩ ወደ ተከፈተው የገቢ ባንክ ሂሳብ

እንዲሁም ከተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ 10% በመቀነስ ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ የመመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ሚዛኑ ዜሮ መሆን አለበት፡፡ አካውንቱም ምንም አይነት ገንዘብ ሊቀመጥበት አይገባም፡፡

(መ) ቅ/ጽ/ቤቶቹ ሰብስበው በአደራ የባንክ ሂሳብ ያስገቡትን የክልሎች የገቢ ድርሻ ባለድርሻውን በዝርዝር በመለየት ገቢው ከተሰበሰበበት ወር መጨረሻ ጀምሮ በአስር ቀን ጊዜ ውስጥ ለገቢ ሂሳቦች ዳይሬክቶሬት በተከፈተው የአደራ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

(ሠ) የባለሥልጣኑ መ/ቤት የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ አደራ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገውን የክልሎች የገቢ ድርሻ አዳምሮ በማጠቃለል በየወሩ ለሚመለከተው ክልል ያስተላልፋል፡፡

(ረ) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሰብስበው ወደ ፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሣብ ገቢ ያደረጉትን ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባንክ ሂሣብ፣ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሣብ ገቢ ያደረጉትን ወደ ከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የባንክ ሂሣብ ወዲያውኑ ያስተላልፋሉ፡፡

## 8. በቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበ እና የተላለፈ ገቢ ሂሳብ አመዘጋገብ

1) የማይክሮ ግብር ከፋዮች /ወረዳ/ ቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ ሲሰበሰቡና ሲያስተላልፉ፡-

(ሀ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ግብር/ታክስ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት ገቢዎች የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በመጠቀም ሲሰበስቡ ሂሣቡን እንደሚከተለው ይመዘግባሉ፡-

| | | |
|---|---|---|
| *በሳጥን /4101/* | *ዴቢት* | |
| *ገቢ /በገቢ አርዕስት/* | | *ክሬዲት* |

(ለ) በየዕለቱ የተሰበሰው ገቢ በየገቢ አርዕስቱ ተለይቶ በገቢ ማጠቃለያ ቅጽ ተጠቃሎ ለክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተረካቢ ዝግጁ ይደረጋል፡፡

2) በየክፍለ ከተማው የተደራጁት የአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ ሲሰበስቡና ሲያስተላልፉ የሂሳብ አመዘጋገቡ እንደሚመለከተው ይሆናል፡፡

(ሀ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ግብር/ታክስ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት ገቢዎች ሲሰበስቡ፡-

| | | |
|---|---|---|
| *ሳጥን /4101/* | *ዴቢት* | |
| *ገቢ /በገቢ አርዕስት/* | | *ክሬዲት* |

(ለ) ከማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ (Summery Receipt Voucher) በመጠቀም ገንዘብ ሲረከቡ የሂሳብ አመዘጋገቡ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| *ሳጥን /4101/* | *ዴቢት* | |
| *ገቢ /በገቢ አርዕስት/* | | *ክሬዲት* |

(ሐ) በየዕለቱ ከግብር/ታክስ እና ከማዘጋጃ ቤት ገቢዎች የሰበሰቡትን እንዲሁም ከማይክሮ ቅ/ጽ/ቤቶች የተረከቡትን ከሳጥን ወጪ አድርገው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሳብ ሲያስተላልፉ የወጪ ሰነድ በመጠቀም፡-

| | | |
|---|---|---|
| *የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሳብ* | *ዴቢት* | |
| *ሣጥን /4101/* | | *ክሬዲት* |

(መ) በወኪሎች አማካይነት ከሌሎች ክልሎች እና ፌዴራል ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ተደርጐ ለቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ሲደረግ የገቢ ደረሠኝ በመጠቀም፡-

| | | |
|---|---|---|
| *ሳጥን /4101/* | *ዴቢት* | |
| *ተከፋይ ሂሳብ /5026/* | | *ክሬዲት* |

(ሠ) ከላይ በተራ ፊደል "መ" መሠረት ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አደራ የባንክ ሂሳብ የወጪ ሰነድ በመጠቀም ገቢ ሲደረግ፡-

| | | |
|---|---|---|
| *አደራ ባንክ ሂሳብ* | *ዴቢት* | |
| *ሣጥን /4101/* | | *ክሬዲት* |

(ረ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ ወደ ከተማው አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የባንክ ሂሳብ የወጪ ሰነድ በመጠቀም ሲተላለፍ ፡-

*ዝውውር /4009/* *ዴቢት*
*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ*
*የባንክ ሂሳብ* *ክሬዲት*

(ሰ) ከሌሎች ክልሎች እና ፌዴራል ግብር ከፋዮች ተቀናሽ ተደርጐ በቅ/ጽ/ቤቱ የአደራ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገው ገንዘብ ድርሻ ወደ ዋናው መ/ቤት ገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የፌዴራሉ ወደ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የወጪ ሰነድ በመጠቀም ሲተላለፍ ፡-

*ተከፋይ ሂሳብ /5026/* *ዴቢት*
*አደራ ባንክ ሂሳብ* *ክሬዲት*

3) የፌዴራል ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መካከለኛ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች የገቢ አሰባሰብና ትልልፍ ሂሳብ አመዘጋገብ፡-

(ሀ) ግብር/ታክስ ወይም የማዘጋጃ ቤት ገቢ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሠኝ በመጠቀም ሲሰበስቡ

*ሳጥን /4101/* *ዴቢት*

- *ገቢ በገቢ አርዕስት /1000 - 1799/* *ክሬዲት*
  */ከፌዴራልና ከአዲስ አበባ ግብር ከፋይ የተሰበሰበ/*
- *ተከፋይ ሂሳብ /የሌሎች ክልሎች/ /5026/* *ክሬዲት*
- *ተከፋይ ሂሳብ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ /5058/* *ክሬዲት*

(ለ) የፌዴራል መንግስት እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ገቢ የሚሰበስቡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከሰበሰቡት ገቢ ውስጥ ባለድርሻውን የሚለዩበት በኮምፒዩተር ሲስተም የተደገፈ አሠራር ስራ ላይ ይውላል፡፡

(ሐ) የተሰበሰበው ገቢ ከሳጥን ወጪ ሆኖ በቀጥታ ወደ ፌዴራል መንግስት የባንክ ሂሳብ ሲገባ (የወጪ ሰነድ በመጠቀም)፡-

የፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሳብ /4103(1) ዴቢት
4101/ሳጥን/ ክሬዲት

(መ) የተሰበሰበው ገቢ ከሳጥን ወጪ ሆኖ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ገቢ የባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ(የወጪ ሰነድ በመጠቀም)፡-

*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሳብ /4103(2) ዴቢት*
*4101/ሣጥን/ ክሬዲት*

(ሠ) የተሰበሰበው ገቢ ከሳጥን ወጪ ሆኖ ወደ መመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ ሲገባ (የወጪ ሰነድ በመጠቀም)፣

*ቼክ መመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ /4103(3) ዴቢት*
*4101/ሳጥን/ ክሬዲት*

(ረ) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመመንዘሪያ ባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ ባለድርሻውን በመለየት ወደ የባለድርሻው ባንክ አካውንት ሲያስተላልፉ (የወጪ ሰነድ በመጠቀም)

I. ከመመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ ወጥቶ ወደ ፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ፡-

*የፌዴራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሳብ 4103(1) ዴቢት*
*መመንዘሪያ ባንክ አካውንት 4103(3) ክሬዲት*

II. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢ ድርሻ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ፡-

*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሳብ /4103(2) ዴቢት*
*የመመንዘሪያ ባንክ አካውንት 4103(3) ክሬዲት*

III. ከመመንዘሪያ የባንክ ሂሳብ ወጥቶ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ተቀንሶ የተቀመጠው ገንዘብ ለዚሁ ወደ ተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ሲደረግ፡-

*የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ /4103(4) ዴቢት*
*የመመንዘሪያ ባንክ አካውንት /4103(3) ክሬዲት*

IV. ከክልል ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ ገቢ ከመመንዘሪያ ባንክ ሂሳብ ወጥቶ ወደ ቅርንጫፍ ቅ/ጽ/ቤቱ አደራ የባንክ ሂሳብ ገቢ ሲደረግ፡-

*የአደራ የባንክ ሂሳብ 4103(5) ዴቢት*
*የመመንዘሪያ ባንክ አካውንት 4103(3) ክሬዲት*

V. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ ወደ ከተማው አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲተላለፍ፡-

*ዝውውር /4009/ ዴቢት*
*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ የባንክ ሂሣብ/4103(2) ክሬዲት*

VI. የፌደራል መንግስት ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ትሬዥሪ አካውንት ሲተላለፍ፡-

*ዝውውር /4009/ ዴቢት*
*የፌደራል መንግስት ገቢ የባንክ ሂሣብ /4103 (1) ክሬዲት*

VII. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተከፈተው የአደራ ባንክ ሂሳብ ወደ ገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አደራ ባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ፡-

*ተከፋይ ሂሳብ ዴቢት*
*የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አደራ ባንክ ሂሳብ 4103(5) ክሬዲት*

VIII. ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ከተከፈተው የባንክ አካውንት ወጪ ሆኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ክፍያ ሲፈፀም

*ተከፋይ ሂሳብ ለተጨማሪ እሴት*
*ታክስ ተመላሽ /5058/ ዴቢት*
*ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የተከፈተ ባንክ ሂሳብ 4103(4) ክሬዲት*

## 9. የሦስተኛ ወገን ገቢ አሰባሰብ፣ ትልልፍና ሂሣብ አመዘጋገብ

1) የሦስተኛ ወገን ገቢ አሰባሰብ፣ ትልልፍና ሂሣብ አመዘጋገብ እስከ 2003 በጀት አመት መጨረሻ አሁን ባለው አሠራር መሠረት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

2) ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ፡-

(ሀ) ለሦስተኛ ወገን ገቢ አሰባሰብ አሁን በየክፍለ ከተማው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ስም የተከፈተው የባንክ ሂሳብ ተዘግቶ በየክፍለ ከተማው በተቋቋሙ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ስም የባንክ ሂሳብ ይከፈታል፡፡

(ለ) የሦስተኛ ወገኖች /ባንኮች/ ባለሥልጣኑን ወክለው የሰበሰቡትን ገቢ በአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ስም ወደ ተከፈተው ከላይ በተራ ቁጥር 9.2 (ሀ) በተጠቀሰው የባንክ አካውንት ገቢ ያደርጋሉ፡፡

(ሐ) ባንኮች /ሦስተኛ ወገኖች/ ሰብስበው በአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የባንክ አካውንት ገቢ ያደረጉትን ገንዘብ ወደ ከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያስተላልፋሉ፡-

(መ) ቅ/ጽ/ቤቶች በሦስተኛ ወገን ስለተሰበሰበው ገቢ መረጃ በማሰባሰብ የተሰበሰበውን ገቢ በየገቢ አርዕስቱ እንደሚከተለው ይመዘግባሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| *የሦስተኛ ወገን ገቢ የባንክ አካውንት* | *ዴቢት* | |
| *ገቢ /የገቢ አርዕስት/* | | *ክሬዲት* |

(ሠ) ቅ/ጽ/ቤቶች ለሦስተኛ ወገን ገቢ አሰባሰብ ከተከፈተው የባንክ አካውንታቸው ገንዘብ ወጪ ሆኖ በቀጥታ ለከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መተላለፉን የሚገልጽ ማስረጃ ሲደርሳቸው ሂሳቡን እንደሚከተለው ይመዘግባሉ፡-

| | | |
|---|---|---|
| *ዝውውር /4009/* | *ዴቢት* | |
| *የሦስተኛ ወገን ገቢ የባንክ አካውንት* | | *ክሬዲት* |

## ክፍል አራት

## <u>የሪፖርት አቀራረብ</u>

### 10 ወርሃዊ የሪፖርት አቀራረብ

1) ከከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ተቀናሽ የተደረገ የሥራ ግብር ሪፖርት አቀራረብ

(ሀ) የክፍለ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ከክፍለ ከተማው የመንግስት ሠራተኞች ተቀናሽ ስለተደረገ የሥራ ግብር ሪፖርት አዘጋጅተው ለየክፍለ ከተማው አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ወሩ በተጠናቀቀ እስከ ሁለተኛው ቀን ድረስ ያቀርባሉ፡፡

(ለ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከማዕከል ሴክተር መ/ቤቶች ሠራተኞች ተቀናሽ ስለተደረገ የሥራ ግብር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወሩ በተጠናቀቀ እስከ ሁለተኛው ቀን ድረስ ያቀርባል፡፡

(ሐ) ለኮንትራት ሠራተኞች ከሚከፈል ደመወዝ ላይ እንዲሁም ለሠራተኞች ከሚከፈል ሌላ ጥቅማ ጥቅም በገንዘብ ተቀናሽ የሚደረግ የስራ ግብር የክፍለ ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ቀንሰው በማስቀረት በየክፍለ ከተማው ለሚገኙ የአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም የማዕከል ሴክተር መ/ቤቶች ለአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ገቢ ማድረግ ያለባቸው ስለሆነ በዚህ መልክ የተሰበሰበ ግብር በዚህ ተራ ቁጥር ፊደል “ሀ” እና “ለ” በተገለፀው ሪፖርት ውስጥ አይካተትም፡፡

(መ) የክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ከላይ በተራ ፊደል “ሀ” እና “ለ” መሠረት ተዘጋጅተው የሚቀርቡላቸውን የስራ ግብር ሪፖርቶች በራሳቸው አማካይነት ከተሰበሰበው ገቢ ጋር በማዳመር ቀጥሎ በተመለከቱት የገቢ ዕቅድ ክንውን እና የገቢ ሂሳብ ሪፖርቶች ውስጥ አጠቃለው ያቀርባሉ፡፡

2) **የገቢና ወጪ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት አቀራረብ**

(ሀ) የማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የሰበሰቡትን ገቢ በተመለከተ ወሩ እንዳበቃ በ2 ቀናት ጊዜ ውስጥ የገቢ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ያቀርባሉ፡፡

(ለ) የአነስተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በወር ውስጥ የተሰበሰበውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የፌዴራል መንግስትና የክልሎችን ገቢ በመለየት፣ እንዲሁም በስራቸው ከሚገኙ የማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች /ለክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች/ ሪፖርት ጋር በማጠቃለል ወሩ እንዳበቃ በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ የገቢና ወጪ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለባለሥልጣኑ የዕቅድና የአፈፃፀም ክትትል ዳይሬክቶሬት እና

ለቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ለክፍለ ከተማው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡

(ሐ) የዕቅድና የአፈፃፀም ክትትል ዳይሬክቶሬት ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበውን የፌዴራል መንግስት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በአደራ የተሰበሰበ የሌሎች ክልሎች ገቢ ለይቶ በማጠቃለል፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማን የታክስ አስተዳደር ወጪ በተመለከተ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው ክፍሎች እና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወሩ እንዳበቃ በ10 ቀን ጊዜ ውስጥ ይልካል፡፡

3) **የገቢና ወጪ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ**

(ሀ) የከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በወር ውስጥ የተሰበሰበውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የክልሎች እና የፌዴራል ገቢ በመለየት እንዲሁም በስራቸው ከሚገኙ የማይክሮ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች /ለክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች/ ጋር በማጠቃለል ወሩ እንዳበቃ በቀጣይ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቅጾችን በመሙላት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

i. ገቢን በመሂ/21 ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ
ii. ወጪን በመሂ/22 ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣
iii. የገንዘብ ዝውውርን በመሂ/24 ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣
iv. ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ በመሂ/25 ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣
v. ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ በመሂ/26 ሪፖርት በተናጠል ይሰራና በሂሳብ ማመዛዘኛ መሂ/27 /Trial Balance/ ተዘጋጅቶ ሪፖርቱ ይተላለፋል፡፡

(ለ) የባለሥልጣኑ የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና የሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበውን የፌዴራል መንግስት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የሌሎች ክልሎች የገቢ ድርሻ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ የታክስ አስተዳደር ወጪ በየወሩ በማጠቃለል ሪፖርት

አዘጋጅተው ለባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ያስተላልፋሉ።

11. <u>መመሪያው የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ 02/07 ቀን 2003 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር